❖

ማጥሞች

❖

ቅዱሷ ቀን

የእሳት ረመጥ
በሆዴ ውስጥ ሲርምጠመጥ
ነበልባል ሆኖ አይነድ
ወይ ወደ አመድ አይለወጥ
እንዲሁ ጎን ለጎኔ እንደሽል ሲገላበጥ
እልተነፍስ አልናገር
ከሰው መንጋ ሰው አጥቼ
እንዲሁ ሳብሰለስል ለብቻዬ ተጎልቼ
ሰው አገኘሁ ብርቅዬ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተመርቼ።
አይ ርብቃ እንደአጥቢያ ኮከብ ተፈንጥቃ
በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ተደብቃ
አገኘኋት በቀን በሌሊት አሽብርቃ
        ያረገዝኩትን ምጣኔ አምጣልኝ
        የመገለ ቁስሌን አፍርጣልኝ
እንደበቴ ያቃተውን በእንደበቷ ተናግራልኝ
እንደአዋቂ አባይ ጠንቋይ የልቤን ጠልቃ አውቃልኝ
        ወይ ርብቃ
እንደአጥቢያ ኮከብ ተፈንጥቃ
ለካም አለ ቀን ከቀን ሁሉ
        የቀን ቅዱስ
ቅባ ቅዱስ የሚያላብሲ።
እንደመላእከት ወርዳ ወርዳ

ድንገት ምድር ላይ አርፋ
እንደነቢይ ትንቢያ ተንቢያ
የውስጤን ስትነግረኝ መንጥራ መነጣጥራ
ወይ ርብቃ
እንደ አጥቢያ ኮከብ ተፈንጥቃ
በስመ አብ ብለው የማይርቀኝ
የማይለቀኝ
የማይሸሸኝ
ያ ቀንዳም ሴጣን አብሮ ያደገኝ
ምቀኝነት የቅናት ዛር
አሉባልታ ወረኛነት
በሰም ግዞት ሆድ ባዶነት
ነገን ሳይሆን ትላንትን እያዜሙ
ተስፋ ባዶ ትዝታን ብቻ የሚያልሙ
ከአጅ አይሻል ዶማ አንዱ ባንዱ
ሲያፌዝበት 1 ሲስቅበት
ሲሄዱ የሚከተል እንደ ጥላ
የማይልቅ ጨረጠገን አመኬላ
ጊዜ የማይሽረው ጉድ
ከትውልድ ትውልድ የሚወለድ
እርስ ብርስ ስንናከስ ስንባላ
እንደግመል ሽንት አድገታችን ወደኋላ
ይኸው ነው አብሮ ያኖረኝ
ያሳደገኝ የማይለቀኝ.... የማይርቀኝ

ያሳሰበኝ ያበሳጨኝ
ሰው ያስፕኝ.....
ይቺ ቀን ግን የቀን ቅዱስ
ተላብሳልኝ መንፈስ ቅዱስ
አመጣች ሰው ከሰው መንጋ
ቃሏ ልቤን የምትነካ
ርብቃ
አዎ ርብቃ
እንደ አጥቢያ ኮከብ ተፈንጥቃ
የሆዴን እንደ ነብይ አወጣችው
የመገለ ቁስሌን ነካካችው
የበለዘ ጎኔን እሻሸችው
የተጣደ ምጤን አማጠችው

ኸረ እናንትዬ

ኸረ እናንተየ አይጣልባችሁ
የጣለብኝን ፍርዱን አይታችሁ።
የሰው ጉድ የእንግዲህ ልጇን
አቅፌ ሳየው አይን አይኗን
ፍቅር ላይ ወደቅሁ በቁሜ
ጥንብ አንሳው ጥንቤን ለቅሜ።
ሾካካ አንዘርት ሹል እግር
ዱልዱም እጅ የምትከረከር
ተሠርቶ አያምር ፀጉሯ
ተፍቆ አይፀዳ ጥርሷ
ሱሪዋ የተዛነፈ.....
አያምር ጉርድ ቀሚሷ
ኸረ እናንተየ አይጣልባቹ
የጣለብኝን ፍረዱ አይታችሁ
እግሮቿ ያጋን ወጥንጩት
የቅንድብ ፀጉር የሌላት
የሰው ግም ከእኔ ጥሎብኝ
ልምት ነው አሷውን ወድጃት
ፀባይዋ ከእኔ ላይ ውሻ
ለሌላው ምትስቅ በጥቅሻ
ውልቻማ ሰልባጅ መቁሻሻ
እንደጅብ ምትሄድ በእንክሻ

ኸረ እናንተየ አይጣልባችሁ
ይጣለብኝን ፈርዱ አይታችሁ
ሹልክልክ የአልጋ ውስጥ አይጥ
ቅንዝንዝ ቀማሽ ሸርሙጣ
እንደባብ በልብ ተሳቢ
ሴስኛ ጉዳም አይን አውጣ
ኸረ እናንተየ አይጣልባችሁ
የጣሉብኝን ፍርዱን አይታችሁ
ከወሬ ወይ ከጨዋታ
የራሷ የሌላት ከቶ
ገልብጣ የምታስተጋባ
ቀልቀሎ ገደል ማሚቶ
የወደድካት ምናት ብትሉኝ
ይኸችው ናት የሰው ጭራቋ
ስሰቃይ ባይኗ እያየች
ማይገባት የፍቅር ቋንቋ።

እኔን ያሉ ወንድ

እኔን ያሉ ወንድ
ጽንስ ሽሌን ነበር ማስወረድ
በብልጭልጭ ዓለም ተዘፍቄ
　　በውሸት መጥምቆ ተጠምቄ
　　ደፍሬ ሳይሆን ፈርቼ
　　የግዴን ምኖር ሰልቺቼ
　　ህይወት ልግፋ እስከመቼ?
ኧረ እኔን ያሉ ወንድ
ጽንስ ሽሌን ነበር ማስወረድ
በቃህ እንዳይለኝ መከራው በእኔ
ማየት ሲያምረኝ አይኔን ባይኔ
ላገናኝ ለዥን ከስኔ
በእርቃን አከሊል ዳማ
ሳስጠጋ መንፈስ ከጎኔ
የወንድ ለንፋጣ ቢሏችሁ
እኔ እዚሁ አለሁላችሁ
ተደፍኖ ማያልቅ ቀዳዳ
ተከፍሎ የማያልቅ ዕዳ
የሴት ልጅ ጉያ አማረኝ
ልቤ ሽንጦ አስቸገረኝ
ኧረ እኔን ያሉ ወንድ
ጽንስ ሽሌን ነበር ማስወረድ:

ሲነጋ ወደመከራ
መሽቶ ቤት ሲሄድ መከራ
የማይታመነውን ሳምነው
ስሸንግል ስለምነው
እኔ እየወቀጥኩት ሌላ ሲሻ
የሌለው ዱካ መድረሻ
ደግሞ እኔኑ ሲያመጣ
መቅኔን መጥምጦ እየጠጣ
12 ሰአት ሠርቼ
ከእውደ ውሸት ሰዎች
አረፍትና እውነት አጥቼ
የምንከራተት መከረኛ
ዝከረ ምንዱባን እሰረኛ
በራሴ ለራሴ ስፈርድበት
የግፍ ጦርነት ሳውጅበት
አይኔን ባይኔ ልይ ብየ
እንዳላየው ተከልክዬ
ከጉድ ጉድጓድ ስጎደጉድ
ተጎድጉጄም ሳልወደድ
ኧረ እኔን ያሉ ወንድ
ጽንስ ሽሌን ነበር ማስወረድ
　　በጨለማ መንገድ ጀምሬ እንደጀግና
　　በዚያ ላይ ሰማይ ደምኖ
　　ከዋከብት እንደ እውነት ተሸፍነው

እግሬና ልቤ ማረፊያ አጦ
ጆሮዬ ኮሽታን አድምጦ
ብርክ ዙፋኔ ላይ ነግሶ
ራዕይ በእንቅፋት እንክሶ
ልቤ በከሀዲ ተነክሶ
በመንታ ምላሷ ለፍልፋ
ሌላ ስታልም እኔን እቅፋ
ከሣት ውዬ ሣት ላይ አረፍኩ
ተቃጥዬ ተንገበገብኩ
በውሸት ፍቅርዬ ስሸሞነሞን
ሥስል አብሬ ቢላዋን
ራሱን ባለጸዳ ሳሙና
ያፀዳኛል ብዬ ለገና
ባለገመናው ከገመና
ዳግም ስወድቅ እንደገና
ኸረ እኔን ያሉ ወንድ
ጽንሰ ሸሌን ነበር ማስወረድ
የፈጪ ልጅ እኔ
ወፍጮ ላይ ለመንኩ አድሜ
ውሎዬ ከባርነት
እዳሬ በባርነት
እምቢኝ አሻፈረኝ እንጃ
እነሳለሁ ጠመንጃ

አላለም ያኔ አባቴ
በር ከፋቹ ለጥቃቴ
እሱም ውሽታም ነፍራቃ
ከእናቴ ጉያ ያልንቃ
ምን ላይ ነው ወንድነቱ
እኔን ለመከራ ማምጣቱ?

ምነው ለእኔ

አቤቱ ሆይ ሰማኝ አንተ
የሰማይ የምድሩ ባለቤት
አጋጭተህ አፋጭተህ
ደጋ ከቆላ እናፍሰህ
የሰው ድርሻ እጣ ፋንታ
ከአንዱ ለሌላው ደራርበህ
ምነው ለኔ ለፆመኛ
ለአይን እንክርትት የዳረግከኝ
ከዛሬ ነገ ይሻላል ብዬ
ብፋጠጥም ከዕድል ቀኔ
ከዚህ ሁሉ ከፈጠርከው
ምነው እጣህ አንዲት ለኔ
ከአመል አመሌ ተዘባርቆ
የሄዋን ጠረኗ ከኔ ርቆ
ተፈጥሮ ቸሯን ነፍጋኝ
ከልሳኔ ቃላት ደርቆ
ከእምናው ዘንድሮ ሳይለወጥ
ለከርሞም ያለራዕይ ስቀመጥ
የኔን ነጥቀህ ተሳስተህ

ከየት ይሆን ያደረስካት
ያስረገዝካት ያስወለድካት
ያፋታሀት ያስቀየምካት

የእሷው ጠፍቷት ሆድ ብሶባት
ግራ እንደኔ ያጋባሀት
አንስተህ ካገር አገር
አስኮብልለህ ያጠፋሀት

በህልም ጨረፍታ ተመልከታኝ
በህልም ጨረፍታ አጫውታኝ
በእውነቱ ግን ማታገኘኝ ማላገኛት
ከርታታዬን የት አረካት
አቤቱ ሆይ ሰማኝ አንተ
የሰማይ የምድሩ ባለቤት
ማናት ከቶ የኔ ፀዳል
አፍቃሪዬ ደም ገምቦዬ
የህይወት ፀዳል አለኝታዬ
የባህር መቅረዝ ዋስትናዬ
የቷ ትሆን የእኔ ድርሻ
ሚጣፍጣት የእጅ ጉርሻ
ከት ብላ ስትስቅልኝ
ሹክሹክታዋ በጆሮዬ ሲወርድልኝ
በፍፁም ደስታ ምሰምጥበት
በጠረኗ ምታሽበት
በጣቶቿ ተዳብሼ
እንገቷ ውስጥ ተሸጉጬ
አይኔን ከአይኗ አጋጭቼ
የመንፈስ ምግቤን ትንፋሿን በትንፋሽ አስገብቼ

በቀልድ ጥፊዋ ተመትቼ

እንደ ልጅነት ንፍርቅ ብላ

ንፍርቅ ብዬ ተነፋርቀን

ቅልጥ ብላ ቅልጥ ብዬ

ተቀላልጠን

የሚያምረውን ፀጉሯን ፈልሸባት ተበሳጭታ

እንደገና ስሰራላት ተደስታ

ሀያው እንዲሁ ለዘለዓለም

ሳትቀየም ሳልቀየም

አቤቱ ሆይ ሰማኝ አንተ

የሰማይ የምድሩ ባለቤት

ይቺውን ለኔ ያልካትን

ዛሬውኑ ብትሰጠኝ ምናለበት።

ል ብ ስ

ልብስን የፈጠረ ይሰበር እጅ እግሩ

የሰው ልጅ በራቁት ነበረ ማማሩ

ለምጣሙ እከካሙ በልብስ ተሸፍኖ

እስከ ጉዳጉዱ ሲተራመስ አብሮ

ሰው መሳይ በሸንጎ በልብስ ተደራርቦ

ጎቢጥ ከመለሎው ይቀመጣል አብሮ

ልብስ ባይለብስ ሰው እርቃን ቢውጣ

አደባባዮች ላይ ፀሀይ እንዴት በወጣ

ልብስን የሰራ ሰው እጅ እግሩ ቢሰበር

ትህምክትና ጉራ ዛሬ አይኖሩም ነበር።

ቃሌ እንዲህ ነበር

ትልቅ ስሆን ሩቅ አገር ሄጄ ....ሩቅ.... ሩቅ
ቁንጥር ችርፍስ ከሚደረግበት ብዙ ገንዘብ ብዙ ፍራንክ
ትንሽ እያለሁ የተመኘሁ ያልኩት ሆኖ ርቄ ወጣሁ
ያኔ በልጅነት ሳየው ቤታችን እፍስሶ
የነ እማማ ታንጉት ቤት ፈራርሶ
አባ ላቂ ልብስ የላቸው ሁሌም ተቀዳደባቸው
የእኛን ቤት እነሱንም ሳያቸው
ለእኛም ለንሱም አዝኜላቸው
ቴፕና ሬዲዮ የለን የላቸው
ታዲያ አስቤ ሩቅ ሄጄ ተሰድጄ
ገንዘብ ዝቁ ገንዘብ ይዥ
የእኛን ቤት ልደፍን
እነ አባ ላቁን ከብርድ ላድን
ብቻ ገንዘብ ዝቁ ገንዘብ ልኬ
ሩቅ መጣሁ በጣም ብዙ ርቄ
ግን ግን መቼ ሆነና
ቃል በቃል ተሻረና
እኔም ልራሴ እያቃሰትኩ.....ገና ....ገና
ቤታችን ሳይሰራ የኔም ቃል ተሽሮ
ያ እሮጌ ቤት ተገኘ ...እኔ ካልኩት ተሽሎ

እኔማ አልኩሽ

እኔማ አልኩሽ ... የውቦች ሁሉ ውብ
ከዚህ ሁሉ ኸልቅ ማህልቅ... ህዝብ አህዛብ
አንድ አንቺን ብቻ.... አጥቢያ ኮከብ
ሆነሽብኝ ልዩ.... በተፈጥሮሽ ስገረም፡፡
.... እኔማ አልኩሽ
የዳሼንቹ እጁ ይሰበር........ ያንቺን ቁንጅና ያልሳለ
በቅራቅንበ ልቡ ጠፍቶ .... ምናሊዛን ገዳይ ያለ፡፡
ገዳይስ ባየ ከዚህ.... የኔይቱን ኀፈር አርበኛ
ባንድ እጇ አንዴ ዳብሳ..... ለዘመናት ምታስኛ፡፡
.............እኔማ አለኩሽ
የታደለው አገኘሽ..... አንቺን በእቅፉ ላይ አወለ
ውብ ከናፍርሽን መጥምጦ... የጭን ደወልሽን ደወለ
እንደ ንብ አበባሽን ቀስሞ..... በደስታ ስካር ዘለለ
እኔ ግን ያንቺ አረሀብተኛ.... በቅናት አካሌ ቆሰለ፡፡
.............እኔማ አለኩሽ
አንቺን ያየሁበት ቀን.... በእርግጥም ያልተባረከች
በሰመመን እቁፉዳዋ... ዘግና እኔኑ የወሸቀች
የፍቅር ዳረንጎቴን ነፍጋ.....ልቤን ለጠኔ የዳረገች
ከህልቆ ቀናት ሣምንታት...... በርግጥም የተረገመች፡፡
.............እኔማ አለኩሽ ባላየሁሽ... ባላወኩሽ
ከሌሎች ላይ ደግነትሽ... በእኔ ላይ ክፉነትሽ
ወደድኩ ባልኩሽ.... እይንህን ላፈር ያሰኘሽ፡፡
ስጋ ለባሽ ሰይጣን..... ለምድር ሲእል የመጣሽ
የመኖሬን ተስፋ አፅልመሽ....ማፍቀሬን አዘቅት የከተትሽ፡፡

አስቴር አወቀ

ስንቱን አስለቀሽው... ስንቱን አስደሰትሽው
ስንቱን አጋባሽው... ስንቱን አፋታሽው፡፡
በተስረቀረቀው.. በእንደበትሽ ቃና
ያንዱ ሲፈርስበት... የሌላው ሲቃና፡፡
ጭልጥ ብሎ በህልም.... በሀሳብ ጎዳና
ባንቺ የቆረቡ...ባንቺ የመነኑ
በመረዋው ድምጽሽ... ታከመው የዳኑ፡፡
ፍቅር ማለት አስቴር... አስቴር ማለት ፍቅር
ያገራችን ዋልታ... ያገራችን ማገር፡፡
ሙዚቃሽን ሰምተው ... ትላንት የተዳሩ
ዛሬም ልጆቻቸው... ታሪክን ደገሙ፡፡
ላኪልን በርሙሴ ... ላኪልን ባርኔጣ
እንሽሞንሞን እና.... ወዳንቺ እንድንመጣ፡፡
በዜማሽ ትካዜ...እንባ ያፈሰሱ
መቆም አቅቷቸው.... ለተልፈሰፈሱ
ይሠራ ሀውልታቸው...በስምሽ ለቀሰሱ፡፡

እንዲያው ግን

ሽጉጥ ባይፈጠር.... ክላሽ ባይፈጠር
መትረየስ ላውንቸር..... B.M ባይፈጠር
አውሮኘላን ባይኖር.... ኑክሌር ባይፈጠር
ሰላይ ደህንነት... ጆሮ ጠቢ ባይኖር
ይቺን አለማቺን.... ይችን የደም ጎራ
በአሜሪካ ፋንታ ... ማን ይመራት ነበር?

በሠፈሩት ቁና

ጥሩም ይሆን መጥፎ ... በሰው ላይ ሰው ሠርቶ
አይቀርም እንዲሁ... አቶው ፈንቶው ውጦ።
ያጭዳል የዘራትን.... ይወቃል ለቅልቆ
ይሠፍራል ድርሻውን... ይወስዳል ለከቶ።
የካደ ይካዳል.... በዳይ ይበደላል
የናቀም ተንቆ... በኋላ ይቀራል
በሠፈረው ቁና ... የጅን ሰው ያገኛል።
ብሰል ፈጣሪ ነው...ዳኛና ፈራጁ
መትሮ የሚያለብሰው..... ሠፊና ቀዳጁ።
በጎም ሥራ ማዶ... ይጠብቃል አልፎ
ለተንኮልም ተንኮል....ይደገሳል መጥፎ።
ብቻ አይቀርም ምንም... መሰፈር በቁና
የሰማዩ ንጉስ ... ድርሻ ሰጭ ነውና።

ነ ብ ሴ

ብከዳሽ ይካደኝ.... ብርቅሽ ይራቀኝ
ከደስታሽ ያውለኝ.... ብስራትሽን ያሳየኝ
ቢያምሽም ያመኛል.... ሁሌ አንቺን ይለኛል
ደስታሽ ለኔ ደስታ... ጀብድሽ ያኮራኛል።
እንባሽም እንባዬ... ኩራትሽ ኩራቴ
አንቺ ብቻ እኮ ነሽ.... ሁለንተናዬ
ነብሴ የኔ ገላ.... እሙየ ወለላ
ማንንም አላስብ.... ፍፁም ካንቺ ሌላ
ነብሴ እውድሻልሁ.... እምልልሻለሁ
አይነጋ ሌሊቱ ...ይኸው እልልሻለሁ
ገና እውድሻለሁ እስከዘላለሙ
ነፍሴ ውዴ ፍቅሬ ... አንቺ እኮ ነሽ እሙ
ነብሴ ነብሴ ነብሴ ብቸኛዋ ነብሴ
ለህመሜ ደራሽ ፈዋሽና አጉራሼ

ሳቅሽ

ሳቅሽ በጣም ያምራል ልብ ይሰረስራል
ሰውነት ይወራል ሰሜትን ይነዝራል
አሁንም ሳቂልኝ በይ ተንከትክችልኝ
የተዝረከርኩበትን ጥርሰሽን ግልጭልኝ
ይውረድ በጆሮዬ ይንቆርቆር በውስጤ
አይኔን ገርበብ ላርገው ግቢልኝ ከሆዴ
ባደንቅሽ ብወድሽ አሁንም ብወድሽ
አልቆርጥ አለ ጥሜ እንደምን ልጥገብሽ
ጋትም አልተነካ አልጎደለም ከቶ
ያድናቆት ፋናዬ ውበት ሞልቶ ተርፎ
አልፋ አሜጋዬ እሳሳልሻለሁ
ምን ጉድፍ ላንሳልሽ በምን ልሰጥሽ ዜሮ
ውብት ከፀባይ ጋር ዋጋሽ ሰማይ ንሮ
ነይ ተቀመጭልኝ ውዷ ዘመናዬ
በጠረንሽ ልስከር ፀዳል አበባዬ
በተስረቀረቀው የሳቅሽ ቅላፄ
ራሴን ሳትኩልሽ ራቀብኝ ድምፄ

አንቺን አመንዝሬ ቢቆጣ ፈጣሪ
ይቅጣ ይፍረድብኝ ይሰብሰብ መስካሪ
ብቻ ይስጠኝ እንጅ ያንቺን ፍርፋሪ
ፍቅርሽን ሽሽቼ አልባልም ፈሪ
ከስቃዮች ሁሉ የምድር መከራ
ፍቅርሽን ማጣት ነው እኔ የምፈራ
ባንቺ ይብላኝ ሀሩሩ ልግባልሽ በረዶ
ይገለጥ ተራራው በኔ ላይ ተንዶ
ደሜን ባፈስልሽ ብከፍልልሽ ፍዳ
ሲያንስብሽ ነው ፍቅሬ ብሰቃይ ብጎዳ
ሳቂልኝ አሁንም ተስረቅረቂ ማሬ
አንቺ ስትኖሪ ነው የመኖር ትርጉሜ።

ቡ ዳ

ቁ ቡዳ በለው ቁ ... የታባቱ

ሰው ይበላል አሉኝ እስከ እግር ጣቱ

ይመስለኝ ነበረ ጠብሶና ቀቅሎ

ሰውን ሰው ሚበላው ስጋውን ዘልዝሎ

ለካስ በአይን ኖሯል ይሚበላው ቡዳ

ለዛውም ወዳጁን አስቀምጦ ባዕዳ

እንግዲህ ልጣላ ከወዳጄ ጋራ

ሳያርደኝ በቁሜ ሳይመዝብኝ ካራ።

ዝንብ

ዝንብ እንደ ንብ ሆና ማር እሰራ ብላ

ከቆሻሻ ርቃ ጣፋጩን ልትበላ

አበባ ፍለጋ ሜዳ ወጣችና

አልጥም አላት ማዕዛው ያበቦቹ ቃና

ዝንብም እንዲህ አለች በንቦች ተገርማ

እቤት ሽታ እየን አበባ ሲገማ

እግር ቢጥላቸው ወደ እኛው ከተማ

የቀሰሙት ነበረ ከሽታው አውድማ

ከቆሻሻ ጠረን ከሚሰነፍጠው

አንድ ቀን ቢቀምሱት ንቦች ሁሉ ዘልቀው

ሰክረው ያብዱ ነበር ቀፏቸውን ለቀው።

እልቅስ

እልቅስ እልቅስ እልቅስ ስሜቴ እልቅስ አልኝ
ናፍቆት ፍቅር ሃዘን ትዝታ ሲንጠኝ
ነብሴ ተንጠልጥላ ልቤን ሲያቃትተኝ
ህይውት ትርጉም አጥቶ ከንቱ ሆኖ ታየኝ
እንዲህ ወደማታ ፀሀይ ስትቀዘቅዝ
ሆዴ ተነፋርቆ ስሜቴ ሲዋዥቅ
ብቸኝነት ጋራ ከኑሮ ሲጋፋ
ይጠፋል ይተናል የሰነቅኩት ተስፋ
እጠጋበት ሳስብ ምደርስበት ሳጣ
የእኔውስ እላለሁ ምበላው ሳላጣ
ውስጤ ሰላም ያጣል ዙሪያዬን እውጥቼ
ሽምጥ ጋላቢ ነኝ ሁሌ መነገደኛ
ልቤ የሚናውዝ እንዳች መተተኛ
መድሃኔት ስፈልግ እንባ ነው ፈዋሽ
ይተናነቀኛል ቀኑ እልፎ ከመሸ።

ሆ ዴ

ከጥዋት እስከ ማታ ምለፋው ላንተ ነው
ሆዴ አይዞህ አትስጋ ዛሬ እንግርሃለሁ
ብታመም ህመምህ ብሞት ያንተም ሞትህ
ብደሰት ብሰራትህ ብጠግብ ጥጋብህ
ለእኔ ያለኸኝ አንተ ላንተ ያለሁህ እኔ
እርቅም ከጎንህ አትራቅ ከጎኔ
ፍቅርን እላፈቅርም አንት እልህ ሆድዬ
ልጅም እንዳልከጅል ምን ልጅ አጣሁ ብየ
ሚስት እና ጉዋደኛ እንዴት ተሞክሮ
ትዳር ካንተ ውዲያ አይጥመኝም ኑሮ
ድግስ ስርግ ካማረኝ እንደግሰና
አሸሸው ገዳዩን ዘፈን እንከፍትና
እኔና አንተ ብቻ በሞቴ በሞቴ
እምጣ ቀለበትከን ይምጣ ቀለበቴ
እልፋ እና እሜጋ ሆኖልን ፍቅራችን
አብረን እንኖራለን በጠባብ ቤታችን።

ሁሉም ያልፋል

እንደጥዋቱ ጤዛ እንደሚጠፋው
ደግሞ እንደነፋሱ እንደሸውሸውታው
ደስታ እና ሀዘን ህልም እና ቅዠት
መኩራት እና ማፈር ማግኘትም ማጣቱ
ቆንጆ ነኝ ጀግና ነኝ እንዲህ ነኝ ማለቱ
ሁሉም በየተራ እየመጡ ያልፉና
ሲቀር ከንቱ ሆኖ የሄዱት ጎዳና
ለካስ ተሰባሪ ሸክላ ነን እቃዎች
ወይ ሰው ዛሬ ንዋሪ ሲነጋ በድኖች።

ገንፎዬ

ካባ እንደደረበች ዘውድ እንደጫነች
ተውባ ተቀብታ መሀል ላይ ቁጭ ያለች
ገላ ልስላሴ ጠረኗ ማማሩ
ያናቷ ላይ ቅቤ ወይ አነጣጠሩ
ተንቧካ ሰንቡከቡክ ሰውነቷ ምቹ
የቀመሷት ሁሉ ያብዳሉ ሰዎቹ
ቀብጥ ቅብጥ ያለች ገንፎ ዘመናይ
በአመት አንድ ጊዜ እንጅ ጧት ማታ አትታይ
አሷን መጋጥ ነበር መላስ አጎንብሶ
ከላይ ሸርጥ ብጤ ከታች ወርቅ አልብሶ
አጠንቅሷት በጣም እጣትም ያማታል
ምላስ ነው ወዳጇ ያቆላምጣታል።

የ ፈ ጠ ር ከ ኝ

የፈጠርከኝ አምላክ የምትኖር በሰማይ
አላይህ እዛ ድረስ ከታች ወደላይ
ምን እልባት ከሰማይ ከደረሰ ድምፄ
የችግሬ ቋንቋ የብሶት ቅላጼ
ስትፈልግ ውሰዳት ያቻትልህ ነብሴ
ጸጋ በረከቱን ሃብትና ንብረቱን
የምወዳት ቆንጆ የወደድኩላትን
ከቤትም ፎቅ ምድር እያለ መኪና
ኑሮዬን ባገሬ ሰብስብ እርገውና
ከወገን ዘመድ ጋር ልኑር እንደገና
ቀኔ ደርሶ ኋላ ስትመጣልህ ነብሴ
እንደፈለግከ እድርጋት ገባሁኝ ኑዛዜ።

ያኔ ወላጆቼ

የጭራሮ በሯን ዝግት አረጉና
እንጀራ በጎመን በልተው ጠገቡና
ጎመን ከውስጥ ገብቶ ቢረባብሻቸው
ልጅ ወልደው ለመሳም እኔ ታይቻቸው
የበሉት በልቷቸው ተጨፍኖ አይናቸው
ሲሰሩኝ አደሩ ደከም ወገባቸው
የጭራሮ ግኝት የጎመኑ ፍሬ
ማረፊያዬን አጣሁ እስከ ዛሬ ዙሬ።

ሀበሾቹ

ወጣን ከሀገር ወጣን እሩቅ ተሰደድን

በየአረብ ሃገሩ ፈረንጅ ሃገር ሄድን

ማግባት መጋባት ነው መውለድ አከታትሎ

አባባላችንም አብሮን ተከትሎ

በዕድል ያድጋል ልጅ በዳቦ በቆሎ

ውስጥ እንደባዘነው ውጭም ከባዘነ

በእድል መኖር ቀርቶ ቂጣውን ካታነ

ያለንበት ከፍቶ ሰማይ ከዳመነ

የት ነው መድረሻችን ከዚህ ከወጣነ።

እንጃ ለሰማይ ቤት

አለማዊ ነኝ ፍፁም አለማዊ

ለሰጋዬ ምኞር ሁሌም ቀዳማዊ

ሀብት ንብረት የምሻ ሆዳም ሆደ ሰፊ

ከብርና ዝና ፈላጊ አነፍናፊ

እድሜ የምፈልግ የምኖር ለራሴ

ደስታ የምሻለት ሁልጊዜ ለነብሴ

እንጃ ለሰማይ ቤት እንጃ ለፍርዱ ቀን

የሚነድ እሳት አለ የሚያቃጥል ነብሴን

እውነት ከሆነ ግን የሚባለው ሁሉ

የገሃነብ ቤቱ ጨለማ ነው አሉ

እወይ እንች ነብሴ ምን ይሻልሽ ከቶ

የሃጢያተኛው ቤት ሲቆይሽ ተከፍቶ

እኔ አለማዊ ነኝ ስጋየ የሚወድ

ከትእዛዙ ሁሉ የወጣሁ ከመንገድ።

ወይ ጉድ ስልጣኔ

ፈረንጅ የሰራውን እየሁ እየሁና

እራሴን ጠየኩት ዞር ብየ እንደገና

ለካስ እንዲያው ሰው ነኝ በልቼ ምተኛ

እየዞርኩ ምለምን የነጮች ጥገኛ

ጥቁር የጠቆርኩት ዝርያ ዝንጀሮ

ስልጣኔ እድገቴ ተባዝቶ በዜሮ

ሰው አለመሆኔን እወኩት ዘንድሮ

ልጇ ላንተ ብዬ

ልጇ ላንተ ብየ ትዳርን ፈርቼ

ቆንጆ ሳይ ርቄ ማፍቀርን ጠልቼ

ጎጆ አልሰራም ብየ ዓለምን ሸሽቼ

ልጇ ላንተ ብዬ አስቤልህ በጣም

ይችን ጠማማ ዓለም ባታያት አይከፋም

ሃጢያት ትሰራለህ ሃሳብ ታስባለህ

ውጥተህ ወርደህ ኑረህ ኋላም ትሞታለህ

እናም ልጇ ስማኝ ላንተ እኔ ሞቻለሁ

አንተን ላለመውለድ

አላገባም ብዬ ብቻየን እኖራለሁ።

አገኘሁ ጓደኛ

ጓደኛ ፍለጋ ስንቱን ማሰኘለሁ

አምና ከታቹ አምና ሰንት አገር ዞሬያለሁ

ጊዜው ደረሰና ቢጤዬን አገኘሁ

እኔ ሰጨስ ያየኝ እሱ ሲጨስ ያየሁ

ተጠያየቅን እና

ሲጋራ ጋር ዛሬ ጓደኛ ሆኛለሁ።

ለቅሶ ድረሱ

ያልሰማችሁ ስሙ መርዶውን ተረዱ

ማቅ ተላበሱና ወደለቅሶው ሂዱ

እውነት ታማ ታማ ሞታ ተቀብራለች

ደረት የሚደልቅ ሙሾ አውራጅ ትሻለች።

ምላስ የወረሰው

ዘልዝሎ ዘልዝሎ ቢወጣ ቢወጣ

ቢከነዳ ማያልቅ ቢታጠብ ማይነጣ

ያንንም ያችንም ሲቀባ የኖረ

ስንቱን አሉባልታ ሰንት ወሬ የፈጠረ

የዛ ሰው ምላሱ ግዝፈቱ ርዝመቱ

ማውራት ከጀመረ ይኸው ሰንት ዓመቱ

ከናቱ ማህፀን ከወጣ ጀምሮ

ከንፈሩን አሹሎ ነገር አቀናብሮ

እንደተሰከረ እንደ አበደ ውሻ

ያን ልክፍ ያን ልክፍ አሳጣ መድረሻ

እርሾ አብሲቱን ጥሎ ምጣዱን ወልውሎ

ነገሩን አቅጥኖ አከንባሎ ጥሎ

ሲጋግር ሲቆልል ይሄም ስራ ሆኖ

ሲያሻው ዛሬ ዘርቶ ዛሬውን ይወቃል

ደግሞ ይተነብያል መጭውን ዘመን ያውቃል

በሰማይ ይበራል ውቅያኖስ ይቀዝፋል

የሚቀረው የለም ሁሉን ያዳርሳል።

...... ወ ረ ኛ ......

ሜ ጨ ቴ

የታባህ አሞራ የታባህ ድመቱ

ወደዚህ አትምጡ ሜጨቴን እትንኩ

ነይልኝ ሜጨቴ ተደበቂ ከኔ

እነሱም በማየት አይግቡ ኩነኔ

የባልዲ ውሃ ተይ በእጄ እጠጣሻለሁ

ሣቂም ያቃጥልሻል ተይ ነግሬሻለሁ

ዙረቱ ይቅርብሽ አትውጭ ብያለሁ

ያማረሽን ሁሉ ነይ እሰጥሻለሁ

ከቆጥም አትውጭ ትወድቂብኛለሽ

እኔ ምተኛበት ጎን ትተኛለሽ

ልቦና ግዢልኝ እባክሽ ሜጨቴ

ዶሮ እንድትሆኝ ነው እንደዚህ መልፋቴ

ሲበሩ አይተሽ ወፎች ለትንደፋደፊ

እንክት ይላል ጎንሽ ተይ አትጣደፊ

እልጠኑም እግሮችሽ ቀጫጭኖች ናቸው

እይኖችሽ እርግብግብ ያንሰፍሰፍ ያላቸው

ጭውጭውታው ዝማሬሽ ሆዴን እየበላ

እደጊ እደጊ እያልኩ ምራቅ በአፌ ሞላ።

አንቺ የጎጆ ቤት ጭስ......

አንቺ የጎጆ ቤት ጭስ አሩቅ የመነንሽው
ከቤት የወጣሽው ሆድሽን የተባሽው
አጋራው ላይ ሆኜ ላይ ስመለከትሽ
ወጣሽ ወደሰማይ እየተግተለተልሽ
ጥላሽት አልብሰሽ የአንባሽን እቋሪ
ጣራ ግርግዳውን አንድም ሳታስቀሪ
ወጣሽ ካገር ወጣሽ መነንሽ በትካዜ
እያቃሰትሽ ዳገት ሳይጨልም በጊዜ
የት ነው መዳረሻሽ ንገሪኝ አንቺ ጭስ
ገዳምሽን ልወቀው እኔም እንድቀሰስ
ጉዳትሽ ጉዳቴ ብሶትሽ ብሶቴ
በደልሽ በደሌ አጦትሽ አጦቴ
ጭንቀትሽ ጭንቀቴ ስሜትሽ ስሜቴ
ተከፍተሽ መትነንሽ አዝኖልሻል ሆዴ
ለእኔስ ማን አለልኝ አንቺ ነሽ ዘመዴ
እኔም ተቃጥየ ነድጀልሻለሁ
ጥላሽት ለብሼ መሄጃ አጥቻለሁ
ከመነኮሽበት አመንኩሽኝና
አብሬሽ ልደበቅ ሁሉን ልተውና
ጭስየ ጭሳለም አንቺ ቆራጥ ጀግና
ነደሽ አልቀረሽም የታባቱሰና።

ቀየው እንዴት ዋለ.....

ይሰማል ወይ ሃሎ አብሮ አደጉን ጓዴ
እንዴት ናት ታታየ እንዴት ነው እያ ከንዴ
እንዴት ነው መንደሩስ ያደግንበት ቦታ
የማይጠገበው ከቧት እስከ ማታ
እንዴት ናት ምንጫችን ውሃ የዘገንበት
እንዴት ናት ጎጣችን ፀሀይ የሞቅንበት
እንዴት ናት መስካችን ጥጃ የጠበቅንበት
ገና እንኳሊ እንኳላ የተጫወትንባት
ተጣልተን ተፋጅተን የተታረቅንባት
እንዴት ናት ምሳናዋ ጥላ ማረፍያችን
እንዴት ናት ፈጭፋጭት ክረምት መዋኛችን
እንዴት ናት እንጩድባ እንጩት መልቀሚያችን
እንደምነው ሸንታ ዶቅማ መልቀሚያችን
እንዴት ነው ሳሙና በር ሽር ሽር መውጫችን
እንዴት ነው አራዳ ቅዳሜ ገበያውስ
ያ ሁሉ ግርግር ያ ሁሉ ትርምስ
እለች ቤሳ መርፌ ቀረፋ ማስቲካ
የለማኙ ዜማ በግጥም ትረካ
እንዴት ነው ጃንተከል የፍቅረኞች ቦታ
ጎበዝ እና ቆንጆ የጀመሩ ዕለታ
ሚቀጣጠሩበት ተስያት ወደማታ

እንደምንነው እብዱ አበባው ዘላኔ

የሚያነበነበው ግጥምና ቅኔ

አማን ነው ወይ አገር እንደምናት ጎንደር

የብሉ ጠጡልኝ የቆስጣኖች አገር።

ደደብነ

ደደብነ ...ደደብነ... ሸ ዓመት ደነቆርነ

ወይ አላሻሻለ ... ወይ አልጨረሰነ

የእኛ ምጥቀታችን... ጥፋቱ ወኔያችን

የተሰራን ማፍረስ .... ሆኖ እውቀታችን

ስንቱ ጥሎን ሄደ ...ከኋላ ተነስቶ

ኢቃጥሎና ቀብሮ ...የወሬን ድሪቶ

ለ ካ ስ

ለካስ የብደት ውጤት ነኝ የጥድፊያ የችኮላ
የትንፋሽ መአት ጋጋታ የደመነብስ ሥሜት ብቀላ
በራስ መውደድ ስምጫ በፍፁም ልብ ስውረት
በአልህ ምናብ ጦርነት በበስባሽ ስጋ ንረት
በንደዋዛ ሃጢያት ጠብታ በቅፅበት ሆድ ውስጥ ጉብታ
የግድየለሾች ቃርሚያ ልቅምቅም የቀበጦች ጉሰምስም
ጉዶች በህልም ያለሙኝ የቴውኔታቸው ቱሩፋት
የመድረኩ ጭብጥ ትርጉም ለተመልካች ራስ ምታት
የእብደት ውጤት ነኝ እኔ የራስ ወዳዶች አባዜ
የስሜት ሽምጥ ጋላቢ የቧልታ ሞት ኑዛዜ

ባላንጣው

እኔ ሆዴን ሳስብ እሱ ሌላ ሲያስብ
ከወገቤ በታች ከጉልበቴ በላይ
የተቸነከረው የስጋ ቁርጥራጭ
ደግሞ እዳ ሊያመጣ እምጦም ላይችለው
እንዳላየ ሊሆን እኔው ልሸከመው
የስጋ ባላንጣ የሰውነት ጠላት
ላይለቀኝ ተጣብቆ ሁሌ ስጋን ሲሻት
በዚህ በውድ ዘመን ቅርጫ እና ሉካንዳ በጠፋበት ዘመን
ደም ደም የሸተዋል ሽትት ያርገውና ይህ እርጉም
ምናምን
ማደሪያ የሌለኝ ከርታታ ባካና
ጠብ ሳይል ሆዴ አንጉቴ ሳይቀና
የስጋ ሟርተኛ ወገቡ ሳይጠና
አምጣ አምጣ የለኛል ጉማ ጉም ስጋ ምጣት ያምጣውና
ሲያምርህ ይቅር ጓዴ የእኔው መቀናጆ
ስጋን አታገኝም በልተህ ተመስጌን በል እልበትና ሰልጆ።

የዞረበት

የሌሊት ጉርምርምታ የምሽት ጭፈራ ሁዳሴ

ሰው ለሰጋው እንጅ የሚል ጠፍቶ ለነፍሴ

አሰረሽ ምችው

አርስ በርስ ተሟሙቆ በሳብ ታጥቦ ተጠምቆ

እንደ ከፉ ቀን

በቀን ጨለማ እንደተዋጠ

እንዱ ባንዱ ላይ እየወጣ ጠርሙስ ቮድካ እየጨለጠ

እንዱ ከአንዱ እየተጋፋ እያፈጠጠ

አጉተምትሞ ከበሮው እንደ ቢ ኤም ተኩስ እነፍርቆ

የጨለመበትን በጨለማው .... ወቃው አውድማ ለቅልቆ

እሪሪሪሪሪ........ውውውውይ

መከራ እንደወረሰው ....ሃዘን እንደቀመሰው

ማቅ ጠጥቶ ማቅ መስሎ በግፊያ በልፊያ ተቆላልፎ

ያበጠ እዕምሮውን ሊያፈነዳ

እጅ እግሩ ወደፊንጅ ሲዳዳ

እቤት ምሽት ጭፈራ ቤት

የሴት ዳሌ በወንድ ጭን

በአደባባይ ሲንከባለል

.............እልልልልልልልል.........

በባዶ ሜዳ ተዘፍኖ ከልሊታው መለሰ ተለቅሶ

በጨለማ ውስጥ ዳበሳ የሰካርታሞች እበሳ

አየሁ ጉድ ጭፈራ ቤት

ቀን የመሸበትን በሰሊት።

ብቻዬን

ብቻ መኖር ነበር ለመኖር አቅዴ

ከሰው ሁሉ ርቁ ሸሸቼ በዘዴ

ባወጣው ባወርደው ከንቱ ሆነ አሳቤ

እንደኖርኩት ልኑር በሰው ተከብቤ

ድሮ ማውቀው ጫካው ድሮ ማውቀው ጹሩ

ደጋው ውይናደጋው ቁሩና ሀሩሩ

ተራራው ገደሉ ሰው ያልነበረበት

በሰው መንጋ ሞላ ቤት ፎቅ ተሰራበት

ብቻ ሚኖርበት ከየት ላምጣ ቦታ

ሆታ የሌለበት ባለ ሺ ፀጥታ

ኳኳቴና ሁከት ጩኸትና ዋይታ

ማልሰማበት አገር ነበር የኔ እይታ

ከእኔ ቀድሞ ሰው ባድማ አንድ ላይ እብዶ

ጫካውን መንጥሮ ተራራውን ንዶ

ተያዘብኝ ቦታው ከዚህ እስከዛ ማዶ

አ ደ ራ (Facebook) ጓዳኛዬ

ስንቱን አወራን ስንቱን ሰው አማን

በስንት ነገር ጉዳይ ቃል ተገባባን

ፊት ለፊት ላታውቂኝ ፊት ለፊት አላውቅሽ

"ፌስ ቡክ" የሚባል ጉድ እኔኑ አምጦብሽ

ስንት ወራት አልፉ "online" (ላይ) አብረን

ማንም ሳይሰማብን ፍቅራችን ኮምኮምን

ያድናቆት ጋጋታ የፎቶው ብዛቱ

Inboxu ሲከፈት ጎህ ሳይቀድ በጥዋቱ

አቤት ሰውነትሽ ገላሽ ማስደሰቱ

ዕቅዳችን ሩቅ መዳር መኳል ነበር

ፍቅራችሁን በblock እንዲህ ሰምጦ ሲቀር

የሆነውስ ሆነ እደራ ሚስጥሬን

Time lineሽ ላይ ተቀማጭ እንዳይሆን

ሳላይሽ ወድጀሽ ሳታይኝ ወደሽኝ

ብፁእኖች ነበርን ዛሬ ባይፈርድብኝ

ደህና ሁኝ በይ ፍቅሬ የእኔ ምናሊዛ

ልለይሽ እንግዲህ ወሬ ሳላበዛ

አልቀርም በሄድኩት እመጣልሻለሁ

Accaunt እና ስም ፎቶየን ቀይሬ ፍሬንድ እንሁን ብየ

እመጣልሻለሁ.........

ዘመን ተቃጠለ

ነደደ ከሰለ ፍም ረመጥ ሆነ

እንዳልነበር ሆነ ዘመን ተቃጠለ

ትንቢቱ ንግርቱ የተባለው ሁሉ

ነበልባል ነዷዱ መብረቅ ቅልቅሉ

እየተጋጋመ ጥላሸት አልብሶ

ዘመን ተቃጠለ ጊዜም ቀኑ ደርሶ

ድንጋዩም እንጨቱም ብረቱም ያቃጥላል

ምኑ ተጨብጦ ወዴት ይደረሳል

በፍም እሳት ዘመን ምርኩዝም ያቃጥላል

ረመጥ ከረመጥ ተጋጨ ተፋጨ

በልቶ አቃጥሎ ምነው መንደድ ያልሰለቸ።

ህ ል ሜ

አይቸሽ አይቸሽ ውድጄሽ አድንቄሽ

ሰምቼሽ ሰምቼሽ ጧት ማታ ሳስብሽ

በህልሜ ስትመጭ ህልሜን ሳላስፈታ

እንዲሁ በተስፋ ነብሴ ስትፍታታ

መጥቸ ሳወራሽ አንቼም ስታወሪኝ

ወይ እውጥቸ አልነግርሽ ወይ አንቺም አትነግሪኝ

እንዳቺ ሁሉ ጠፍቶ ግራ ስታጋቢኝ

ድንገት ደራሽ ወሬ መርዶ ደረሰና

ደርቄ ቆምኩልሽ እላት እሉኝና

ምን አይነት ፍጡር ነሽ እንዴት ካንቺስ መጣሁ

አንድ አንቺን ብወድሽ አንድ አንቺውን አጣሁ

በጠራራ ፀሃይ እንቅልፍ የወሰደኝ

የዳበሳ ፍቅር ካንቺው ላይ የጣለኝ

መላ ሰውነትሽን በምናብ ያስቃኘኝ

ቅዠታው ህልሜ ያቃዠኝ ያቃዠኝ

አሁንም አሁንም ሚያቃዠኝ ሚያቃዠኝ።

ላኮርፍሽ ነው

ለምቦጬን ልጥል ነው ላኮርፍሽ ነው ዛሬ
ቁልምጥ አምሮኛል ፈሰስ ለበል ማሬ
አልበላም አልጠጣም አልተኛም ልበልሽ
አልሄድም አልመጣም አላነጋግርሽ
አኩርፌያለሁ በቃ ...
እንደልጅነቴ ልጫወት እቃ እቃ
ምን ሆንከብኝ በይኝ ፍቅርየ የእኔ ጌታ
ስታቆላምጭኝ ልይ ያንችን እይታ
ደግሞ እንደሀፃን ልጅ እቅፍ እንደገባ
በጉያሽ ገብቼ ደረትሽ ላይ ላንባ
ምን ሆንከብኝ በይኝ ምን አገኘህ ውዴ
ንኪኝ ልነካካ ክንድሽን በክንዴ
እተኩረሽ እይኝ ያይኔን ውስጥ ብረቱን
እተኩሬ ልይሽ ሚስጥር ውበትሽን
ጉንጭሽን ካናቴ ደገፍ አድርጊና
ደባብሽው ጀርባየን ስሜን ጥሪውና
ትንፋሽ ቢጃሮየ ልቀቂብኝ ፍቅሬ
አቆላምጭኝ ውዴ ታምሚያለሁ ዛሬ

ምግብ አልበላልሽ እንደዚህ አኩርፌ
እያነከሽ አጉርሽኝ ያፍሽኝ ወዳፌ
ውሃውን ፉት ብለሽ አጠጭኝ ልጠጣ
የልሳንሽ ማሩ ወደ እኔ እንዲመጣ
እንገትሽ ውስጥ ልግባ ልማግ ወዘናሽኝ
ሚያሳብደኝ ሳጣው ለዛ ጠረንሽን።

ባንቺ የተነሳ

ምን ያልሆንኩት አለ ባንቺ የተነሳ
አእምሮዩ ዘግም ሰውነቱ ሳሳ
አብድ ሆኜ ወፈፈ ቢለወጥ አመሌ
ከፉ ተባልኩልሽ ተበከለ ስሜ
ሁሉም ይጣላኛል ሁሉም የሰድበኛል
ፀባይህ ከሰው ጋር አይገጥምም ይሉኛል
ይሳሳቁብኛል ይጠቋቆማሉ
እንዳትቀርቡት ብለው ያስጠነቅቃሉ
የእኔ ምለው ለእኔ ውስጤን የሚረዳ
አንድም ሰው የለኝም ከዘመድ ከባዕዳ
ተሰፋዬ አንቺ ነበርሽ የኑሮ ሻማዬ
ቀልጠሽ ካድሽኝና ወጣ ገመናዬ

እርባ ጅራፍ ዓሊ ዓለሙ ሃሰን ሚያዚያ 2008

ፍ ቅ ሬ

ሰሞኑን በህልሜ መጣሽብኝ ፍቅሬ
ናፍቆት አስቃየኝ አስታወስኩሽ ማሬ
ይመሻል ይነጋል ልቤ እንደናወዘ
ትዝታሽ ገርሽቶ ቀልቤ ደነዘዘ
መኖሬ ህልም ሆኖ ይረበሻል ሆዴ
ንፍቅ ስታደርጊኝ ፍቅርየ መውደዴ
ግርማሽ ያ ጨዋታሽ ድቅን ሲል ፊቴ
ስንቱን አስብኩ ባንቺ ሳሳ ሰውነቴ
ትላንት ያሳለፍነው ያን ደጉ ዘመን
እሁን ምን አሰበት ዳግም ቢያገናኝን
ብየ እጨነቃለሁ በሀሳብ በሰመመን

ወርቁን ጣልነ

እንደዋዛ እንደቀልድ ባህሉን በርዘን
አድማሳችን ጥሰን ወንዛችን ተሻግረን
ባዷችን ልንቀር ነው .....
ያያት የቅድመ አያት ባህልና ወጉ
ያስተሳሰረነ ህግና ልማዱ
እነሆ ተናደ ተበተነ ቤቱ
ኩራት አልነበረ በወግ ማረግ መዳር
ሽማግሌ ልኮ ማግባት የጨዋ ዘር
አከብሮ አስከባሪ አገር አስታራቂ
መካር አስተማሪ ከፉ በጎ አዋቂ
ስርቶ አዳር ጎበዝ ሚያበላ ሚያጠጣ
በቃሉ የሚያድር ከጉድ የሚያወጣ
ተብሎ ሰው ተመርጦ ነበረ ጋብቻ
በእነ ደጉ ዘመን ሚጣድ ሰስት ጉልቻ።
ምነው ዛሬ......
ልጅህን ለልጄ የሚባባል ጠፋ
እንደ እህያ ሜዳ ሴት ወንዱ ተላፋ
ብራንባ የወጌን ልጃገረድ ቀረ
የእነ ስልጡን ምጣድ የትም ተሰበር
ልጁም ተወሰደ ማን ይሆን አባቱ
ዋርካው ተቀረጠ ተጠራ በእናቱ

የተናቁ ናቁ ንፍጡን ለቀለቁ
ሳያውቁበት ሰመው በጉንፋን እለቁ
ድመት እንኳ ባቅሟ ያባቷን ሳትረሳ
ፊቷን ትጠርጋለች በምላሷ ልሳ
ወርቁን ጭቃ ጥለን መዳቡን እሰርን
ወደፊት ስንባል ወደ ኋላ ሄድን።

8ኛው ሺ

መሬት ታርሳ ታርሳ ለም አፈሯ አለቀ
ተበልቶ ተበልቶ አለቀ ደቀቀ
ትንቢቱ ድረሰ ሴት ሱሪ ለበሰች
እለማቺን ሰከራ ቀወሰች አበደች
ውንድሙን ወንድሙ ፍርድ ቤት አቆመው
ምሎ ተገዝቶ ተበድሮ ካደው
ጦርነት ነገሠ ባራቱም አቅጣጫ
ሃዘንተኛው በዛ እዛ እዚህ ተንጫጫ
እምነት መነመነች ገንዘብ አምላክ ሆነ
እውነት ከሥማ ጠፍታ ሀሰት ገነገነ
በአንደኛው ሞት አንዱ ከበሮ ደለቀ
ማህይሙ ነግሶ ሙሁሩ ወደቀ
በዘር በሃይማኖት ጥል በቀል ነገሰ
መጨረሻው ዘመን መጣ ገሠገሠ
ሚስት አለቃ ሆና ባል እንገቱን ደፋ
ትልቅ አስታራቂ ሽማግሌ ጠፋ
ሴሰኛ አመንዝራ ገሀድ ወጣ ይፋ
ማፈር ማክበር ቀረ ሜዳ ላይ ተላፋ
መቀመቅ ወረደ የሰው ሰውነቱ
ማገሩ ጎመዘዘ ጠቆረ ወተቱ
እኛ የደረስንበት ይሄ እርጉሙ ዘመን
ዘጠነኛው ሽ ላይ ጉድ አይተን ጉድ ሆንነ

9ኛው ሰይጣን

1ኛው በኩርኩም ነካ አድርጎኝ ሄደ

2ኛው ጥፊ ፊቴ ላይ አውርዶ

3ኛው በዛቻ እየተወራጨ

4ኛው ቴስታ ግንባሬን አጋጨ

5ኛው ምራቅ አይኔ ላይ ረጨ

6ኛው ፀጉሬን ሙልጭ አርጎ ላጨ

7ኛው ነካኝ አገጩን ባጋጨ

8ኛው ንቆ ሳይነካኝ አለፈ

9ኛው ከፋ አለቅ አለ አንገቴን..... አንቆና ቆልፎ እያስለፈለፈ።

ነበሩን - ጎረቤት

ነበሩን ጎረቤት ከሮጥን ሚሮጡ
ከቆመን ሚቆሙ ከሸናን ሚሸኑ
ካነባን ሚያነቡ ካዜምን ሚያዜሙ
ነበሩን ጎረቤት
ሶፋ ስንገዛ አብረውን የገዙ
እናቴ ስታረግዝ አብረው ያረገዙ
በሄድንበት ሁሉ አብረው የተጓዙ
ነበሩን ጎረቤት
ቅን ጥሩ ሰናስብ መጥፎውን ያሰቡ
ስናስከብራቸው እኛን ያዋረዱ
በዶደመው ቢላ ማጅራት ያረዱ
ርቀን ስንሄድ የተከታተሉን
ተው ስነላቸው ምን አደረግን ያሉን
...... ነበሩን ጎረቤት
ልብሳችን ሰንቀድ አብረው የቀደዱ
ቤታችን ስናፈርስ አብረው ያፈረሱ
ስለ እነሱ ሳይሆን ሰለኛ የኖሩ
ነበሩን ጎረቤት እሚፎካከሩ.

ለ ጎ ረ ቤ ቶ ቻ ች ን.........

ነ ጋ

ረዝሞ ረዝሞ ይሄው ነጋ ሌቱ
ለውሶኝ ለውሶኝ ህለምና ቅዥቱ
የተንላበጠው የጎኔም በርታቱ
ያየሁ የሰማሁት ቱማታው ብዛቱ
ብቻ ነጋ ሌቱ
በሠረ ንጋቱ
ጭው ጭው ሲሉ ወፎች ጎህ ሲቀድ ሰማዩ
ከእስር ነፃ ውጣሁ ለቀቀኝ ሲቃዩ
ቀጥቅጦኝ ረግጦኝ ዱካከ አፈራግጦኝ
የእኔ ያልሆነን ሰጥቶ የእኔኑ ወስዶብኝ
እንዴ ቱጃር አርጎ እንዴ ሲያደኸየኝ
ብቻ ነጋ ሌቱ በሠረ ንጋቱ
ሰውን ከመቃብር ፈነቃቅሎ አውጥቶ
እኔ በቁም ሞቼ ሙታኑ ነቅቶ
ይሸኙዋል ቤቱን አብልቶ አጠጥቶ
ብቻ ነጋ ሌቱ በሠረ ንጋቱ
በቀን ተመኝቼ በእውን ያጣኋትን
ያቺን ጋለሞታ
እምጥቶ አሳቀፈኝ በሩቅት ገላዋ
ገላየን ሲያስመታ

ሁሉን ነገር እናውቃለን

ሁሉን ነገር እናውቃለን
ብንናገር እናልቃለን
ከ ሀ እስከ ፐ የዋጥነውን
ቋ ፏ ሯ ሟን ያኘከንውን
ጥርስ አብቅለን ነቅለንበት
ሁሉን ነገር ያወቅነውን
ፈርተን.... ቦክተን....
ይሁን ብለን የተውነውን
ይረር ይትከን ....
ፈልቶ ይትነን
ብለን ወደን የጣድነውን
በምላስ ሆድን ለመጥረግ
ወጣ ገባ ሲደረግ
የምናውቀውን እስተምረው
ጭራሽ ደግመው ሊያደድቡን
ትላንት ያንኑ..... ዛሬም ያንኑ
የዶፍ ናዳ ሚያዘንቡብን
ተዉ አትርዱን
ግን ግን ተውን
አታውሩልን.... አትንገሩን
ሁሉን ነገር እናውቃለን

ብንናገር እናልቃለን
ንሥር አሞሮች ነን
ከሩቅ ሆነን እናያለን
በሌሊት ተጓዥ ጅቦችም ነን
መዘርጠጡን እናውቃለን
እንደ ጅል ....እንደ ቂል ለምታዩን
ሁሉን ነገር እናውቃለን
ብንናገር እናልቃለን።

ብ ለ ን ነው

ፍርሃት

እኔ የአንቺ ጀግና .... ወንዱ አይበገሬ

ውርደትን አልሻም....ሞታለሁ ለክብሬ

አልፈራውም ነብርን.......አልፈራም አንበሳ

አልፈራውም ዘንዶን ....ለነፍሴም አልሳሳ

አልፈራም ጭለማ.......ሴይጣንም ቢያጋሳ

ምንም በይኝ ምንም......ማንንም አልፈራ

ብቻ የማልዋሸሽ.......ከባዱ ፈተና

እኔ ያንቺ ጎበዘ.......እኔ ያንቺ ጀግና

ሰው የሚሉትን አውሬ.......በጣም ነው የምፈራ

........አንቺ የሌለሽበት

አንቺ የሌለሽበት.....ምን ዓለም ታምርና

እንደበቴ እቅጩን......ይናገራል ገና

እንጀራው ተቆርሶ ....ይቅር አይጎረስ

የማር ብርዙ ቀርቦ.....አይጠጣ ይፍሰስ

ምድር እርቃን ትወጣ.....ትከሰል አይደንቀኝም

ጨረቃይቱም ትጥቆር.........ውበቷ አይናፍቀኝም

ያንባርቅ ሰማዮ........መብረቅ እሳት ይትፋ

ውቅያኖስም ይትነን........ከምድር ገጽ ይጥፋ

አንቺ የሌለሽበት.....ምን ዓለም ታምርና

ለመኖሬ ትርጉም ....ለእኔስ ማን ሆነና

እንቺው ነሽ.......አንድ አንቺ

ለሥጋ ለነፍሴ.....ፍፁም የምትመቺ

ፍ ቅ ሬ......

ስሞኑን በህልሜ መጣሽብኝ ፍቅሬ
ናፍቆት አስቃየኝ አስታወስኩሽ ማሬ
ይመሻል ይነጋል ልቤ እንደናወዘ
ትዝታሽ ገርሽቶ ቀልቤ ደነዘዘ

መኖሬ ህልም ሆኖ ይረበሻል ሆዴ
ንፍቅ ስታደርጊኝ ፍቅርየ መውደዴ
ግርማሽ ያ ጨዋታሽ ድቅን ሲል ፊቴ
ስንቱን አስብኩ ባንቺ ሳሳ ሰውነቴ
ትላንት ያሳለፍነው ያን ደጉ ዘመን
አሁን ምን አለበት ዳግም ቢያገናኘን
ብየ እጨነቃለሁ በሀሳብ በሰመመን

ዋጋ **$10.00**